ለ **2022-23** የትምህርት ዘመን

# መመዝገብ



# እንኳን ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በደህና መጡ

## የወላጆች መመሪያ መጽሃፍ

**Arlington, Virginia** ***www.apsva.us***

Arlington Public Schools

# ማውጫ


**የበላይ ተቆጣጣሪው እንኳን ደህና መጡ ........ 2**
**የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮችዎ ........ 3**
**የትምህርት ቤት መረጃ ክፍለጊዜዎች እና የዝውውር ሂደት**
**ለ2022-23 የትምህርት ዘመን ........ 3**
**APS መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ........ 4**
ዶሮቲ ሃም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 4
ገንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 4
H-B ዉድላዋን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም ........ 5
ቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 5
ኬንሞር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 6
ስዋንሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 6
ዊሊያምስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 7
**ልጅዎን ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት መመዝገብ ........ 7**
**የአሁኑ ጊዜ የአርሊንግተን ተማሪዎች ........ 7**
የኮርሶች ምርጫ/የአካዳሚክ እቅድ ማውጣት ........ 7
**አዲስ ተማሪዎች ........ 7**
ልጅዎን ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ........ 7
የጤና መስፈርቶች ........ 8
የሚያስፈልጉ ክትባቶች ........ 8
የሚመከሩ ክትባቶች ........ 8
ስፖርቶች ላይ መሳተፍ ........ **8**
**የመግቢያ ፕሮግራም ምዝገባ መረጃ ........ 8**
መግቢያ ምንድነው? ........ 8
ለ2022-23 የትምህርት ዘመን የምዝገባ ሂደት ........ 8
**ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች እቃሚ መረጃዎች ........ 8**
**ጠቃሚ የድር ማስፈንጠሪያዎች ........ 9**
**ማውጫ ........ 9**
**የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦታዎች እና ወሰኖች ካርታ ........ የጀርባ ሽፋን**


---


አርሊንግተን ዘርን፣ ብሄራዊ አመጣጥን፣ የሃይማኖት መገለጫን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትትን፣ ጾታን፣ እድሜን፣ የኢኮኖሚ ሁኔታን፣ የጾታ ዝንባሌን፣ እርግዝናን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ የዘር መረጃን፣የጾታ ምንነትን ወይም አገላለጽን፣ እና/ወይም የአካል ጉዳትን መሰረት ያደረገ መድልዎን ይከለክላል። ይህ ፖሊሲ ለኮርሶችን እና ፕሮግራሞች፣ ለምክር አገልግሎቶች፣ ለአካል ብቃት ትምህርት እና አትሌቲክስ፣ ለሙያ ትምህርት፣ ለመምህራን እና ከስርዐተ ትምህርት ውጪ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች እኩል ተደራሽ አድርጎ ያቀርባል። የዚህ ፖሊሲ ጥሰት ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ዋና ሃላፊ በ 703 228-6008 ወይም ለሰብዐዊ መርጃዎች ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ በ 703-228-6110 ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

Arlington Public Schools

ጥቅምት 2021

**ውድ ቤተሰቦች፣**

እንኳን ደስ አለዎት! ልጅዎ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ አመት ላይ ደርሷል እናም በቅርቡ ወደ መካከለኛ ደረጃ እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሄድበትን ጉዞ ይጀምራል። አርሊንግተን ውስጥ፣ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ ከሌሎች በርካታ አካዳሚክ አማራጮች ጋር አሳታፊ የሆነ የማስተማሪያ እና በማህበራዊ ደረጃ ደጋፊ የሆነ አካባቢ ስላለን ደስተኞች ነን። ያሉትን አማራጮች ሲያጠኑ፣ የልጅዎን ልዩ ባህሪያት ግምት ውስጥ ያስገቡ። ይህን ማድረግ የልጅዎን ጥንካሬዎች፣ ፍላጎቶች እና የሚያስፈልጉትን ነገሮች የሚያሟላ ትምህርት ቤት እንዲያገኙ ያግዝዎታል።

ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሸጋገር ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የተማሪዎችን የወደፊት እቅዶች እንዲያመቻቹ እና እንደገና ትኩረት እንዲሰጡ እድልን ይሰጣል። የኮቪድ-19 ወረርSኝ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተለውጦ ሊሆን ስለሚችል፣ ከተማሪዎች ጋር ስለ ትምህርት ግቦቻቸው እና የስራ ፍላጎቶቻቸው ለመወያየት ይህ ምርጥ ጊዜ ነው። ተማሪዎች ስለ ራሳቸው ብዙ የተማሩ ሲሆን በወረርሽኙ ወቅት ብዙ ልምድ ነበራቸው፤ አዲስ ፍላጎቶችን አግኝተው ወይም ደግሞ በሚወዷቸው ርዕሶች ላይ ፍላጎት አጥተው ሊሆን ይችላል፣ ይህም ለመጪው የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ሽግግር ለማቀድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሽግግሩን ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች እንከን የለሽ እንዲሆን ለማድረግ በዚህ አለን።

በሂሳብ እና/ወይም በውጪ ቋንቋ ኮርሶችን የመውሰድ እድሎችን በተመለከተ ከልጅዎ ጋር መነጋገር እንዲጀምሩ አበረታታዎታለሁ። ማበረታታት እና ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቁ ነገሮችን እንደሚያሳድጉ እና ልጅዎ ሙሉ አቅማቸው ላይ እንዲደርሱ እንደሚረዳ እናውቃለን። በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አልጀብራ 1ን የሚወስዱ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከፍተኛ ደረጃ ሂሳቦችን እና የሳይንስ ኮርሶችን ለመውሰድ ዝግጁ እንደሆኑ እና በድህረ- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ላይ ለስኬት እንደሚያዘጋጃቸው ጥናቶች ያሳያሉ። በተመሳሳይ፣ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሃገር ውጪ ቋንቋ ጠንካራ ኮርሶችን መውሰድ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለበለጠ የአካዳሚክ ኮርሶችን እንዲወስዱ ያዘጋጃቸዋል። በስተመጨረሻም፣ ይህ የኮርስ ስራ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ እንኳን የኮሌጅ ክሬዲቶችን ሊያስገኛቸው ይችላል።

በልጅዎ ህይወት ውስጥ መመጣጠንን መመስረት እና መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ከስርዐተ ትምህርት ውጪ የሆኑ ተግባራት ክበቦች፣ ስነ ጥበቦች፣ ስፖርቶች፣ ሙዚቃ፣ ወዘተ፣ ለልጅዎ አጠቃላይ ደህንነት ጠቃሚ ሲሆኑ ደህና-የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልምድ እንዳላቸው ያረጋግጣል።

በእቅድ ማውጣት ሂደቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ላበረታታዎት እፈልጋለሁ። በመካከለኛ ትምህርት ቤት፣ የተመደበ የትምህርት ቤት አማካሪ ፍላጎታቸውን እና ለመመረቅ የሚያስፈልጉትን ኮርሶች የሚያንጸባርቅ የስድስት አመት የትምህርት እቅድ ለማዘጋጀት ከልጅዎ ጋር በጋራ ይሰራል። የአካዳሚክ እቅድ ግልባጭ ለግምገማዎ እና ለግብዐትዎ ወደ ቤት ይላካል። ለተማሪ ስኬት እና ደህንነት ምን ምን አይነት ድጋፎች እንዳሉ ለማወቅ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ ከአማካሪ እና ከአስተማሪዎች ጋር ይነጋገሩ፣ እናም ልጅዎ የገለጻቸውን ሃሳቦች እና ፍላጎቶች ያጋሩ። ይህ ሁሉ እቅድ ማውጣት በቀጥታ የልጅዎን የመመረቅ ግቦች እና ከAPS በኋላ የሚወስዱትን ቀጣይ እርምጃቸውን ያተኮረ መሆን አለበት።

በኦንላይን በ[www.apsva.us/engage](www.apsva.us/engage). ከሚገኘው የ2018-2024 APS ስትራቴጂክ እቅድ ጋር ራስዎን እንዲያላምዱ አበረታታዎታለሁ። የስራቴጂክ እቅዱ ሁሉም ተማሪዎች በደህንነቱ በተጠበቀ፣ በጤናማ፣ በፍትሃዊ፣ እና በደጋፊ የመማሪያ አካባቢዎች መማራቸውን እና ማደጋቸውን ያረጋግጣል፣ እናም ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያበረታታቸውን አካታች ማህበረሰብ ያቀርባል።

ወቅታዊ የAPS ዜናዎችን በ[www.apsva.us](www.apsva.us) ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎችን ያግኙ። ስለ አሁኑ የማህበረሰብ ተሳትፎዎ እድሎች መረጃ ያግኙ እና በAPS ድህረ ገጽ "[ከAPS ጋር ይሳተፉ](ከAPS ጋር ይሳተፉ)" የሚለው ክፍል ውስጥ አስተያየት ይስጡ። የማህበረሰብ ግብዐት እና የተቀናጀ ትብብር APS እድገቱን እንዲቀጥል የሚያደርግ እና የተማሪዎቻችንን የወደፊት ህይወት በጎ በሆነ መልኩ የሚቀርጹ ውሳኔዎችን የሚወስን የሂደቱ ወሳኝ አካል ነው። ልጅዎ በAPS ያለው የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልምድ የሚያያሳድግ እና ስኬታማ እንዲሆን ለማረጋገጥ በዚህ አጋርነት ከእርስዎ ጋር ለመስራት በጉጉት እንጠብቃለን።

ከሰላምታ ጋር፣



ዶክተር ፍራንሲስኮ ዱራን፣ Ed.D.
የበላይ ተቆጣጣሪ

# የእርስዎ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች

ሁሉም ተማሪዎች በሚኖሩበት ልዩ የመገኘት/የወሰን ዞን ወደ ተዘጋጀው የአካባቢ ትምህርት ቤቶች እንዲገቡ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። (የልጅዎን የአካባቢ ትምህርት ቤት ለመወሰን በጀርባ ሽፋኑ ላይ ያለውን ካርታ ይመልከቱ፣ apsva.us/boundariesን ይጎብኙ ወይም በ703-228-8000 ይደውሉ።) **የበላይ ተቆጣጣሪው ለትምህርት ቤቱ ቦርድ በሚያደርገው አመታዊ ማዘመን መሰረት** ተማሪዎች ለአማራጭ ትምህርት ቤት/ፕሮግራም ሊያመለክቱ ወይም ዝውውር ወደሚቀበል አጎራባች ትምህርት ቤት ሊዘዋወሩ ይችላሉ።

### አማራጭ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

በካውንቲው ውስጥ ያሉ ሁሉም ተማሪዎች በ **H-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም** ለማመልከት ብቁ ናቸው። የተለየ መገኘት/የወሰን ዞን የለውም፣ እናም የተለየ የቅበላ ፖሊሲ እና ሂደት አለው። **ለ2022-23 የትምህርት ዘመን በH-B ዉድላውን ለማመልከትየአማራጭ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻን ማቅረብ አለብዎት።**

የገንስተን ስፓኒሽ ከፊል ቅበላ እና የሞንቴሶሪ መካከለኛ አመታት ፕሮግራሞች ክፍት የሆኑት በኮርስ ምዝገባ በኩል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስፓኒሽ የከፊል ቅበላ ፕሮግራም ወይም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሞንቴሶሪ ፕሮግራም ላጠናቀቁ ለአሁን የአርሊንግተን ተማሪዎች ነው። ለአርሊንግተን ወይም ለየትኛውም ፕሮግራም አዲስ የሆኑ ተማሪዎች

**ከላይ በተዘረዘሩት በማናቸውም ፕሮራሞች ውስጥ ለተመዘገቡ ብቁ ተማሪዎች የባስ ትራንስፖርት ቀርቧል።**

ለ2022-23 የትምህርት አመት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማራጮች የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ703-228-8000 ላይ ይደውሉ ወይም የAPS ድረገጽን ላይapsve.us/school-optinos "አማራጮችና ዝውውሮች" ወደሚለው ክፍል ይሂዱ።

# የትምህርት ቤት መረጃ ክፍለጊዜዎች እና የዝውውር ሂደት ለ 2022-23 የትምህርት ዘመን

### አማራጭ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

ለ2022-23 የትምህርት ዘመን ለአማራጭ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም የማመልከቻ ጊዜው ከህዳር 1፣ 2021 እስከ ጥር 21፣ 2022 ድረስ ነው።

የአማራጭ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ማመልከቻ ጥር 21፣ 2022 ላይ ምሽት 4 ሰአት ላይ በኦንላይን መጠናቀቅ አለበት። የኦንላይን ማመልከቻውን ለማጠናቀቅ እርዳታ ለማግኘት፣ እባክዎ የእንኳን ደህና መጡ ማዕከልን በ703-228-8000 ያነጋግሩ ወይም፣ የAPS ድህረ ገጽን ይጎብኙ፡*apsva.us/school-options*።

### ወደ አጎራባች ትምህርት ቤቶች ዝውውሮች

ለ2022-23 የትምህርት ዘመን ለአጎራባች ዝውውር የማመልከቻ ጊዜው ከመጋቢት 21፣ 2022 እስከ የካቲት 11, 2022 ድረስ ነው።

የአጎራባች ዝውውሮች ማመልከቻ የመጋቢት 11፣ 2022 ላይ ምሽት 4 ሰአት ላይ መጠናቀቅ አለበት። የኦንላይን ማመልከቻውን ለማጠናቀቅ እርዳታ ለማግኘት፣ እባክዎ የእንኳን ደህና መጡ ማዕከልን በ703-228-8000 ያነጋግሩ ወይም፣ የAPS ድህረ ገጽን ይጎብኙ፡*apsva.us/school-options*።

### ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረጉ የመረጃ ክፍለጊዜዎች

ወላጆች በአካባቢ ትምህርት ቤት እና/ወይም አማራጭ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም የትምህርት ቤት የመረጃ ክፍለጊዜዎች ላይ እንዲገኙ ይበረታታሉ። የትምህርት ቤት መረጃ ክፍለኢዜዎች ወላጆች ስለ ትምህርት ቤቶች የበለጠ እንዲያውቁ፣ የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች እንዲያገኙ፣ እና የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ምንነት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያስችላል።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚያዘጋጁት ቨርቹዋል የመረጃ ክፍለጊዜዎችን ነው። ሁሉም ክፍለጊዜዎች ይመዘገባሉ እና ከቀጥታ ክፍለጊዜው ቀጥለው በኦንላይን ይገኛሉ። የመረጃ ክፍለጊዜ ማስፈንጠሪያዎች እንዲሁ *apsva.us/school-options/middle-school-choices/school-information-sessions/* ላይ ይገኛሉ።

| **የመረጃ ክፍለጊዜዎች** | |
|---|---|
| **ዶሮቲ ሃም**<br>703-228-2910 | ጥር 20፣ 2022<br>6:30 ፒ.ኤም |
| **ገንስተን**<br>703-228-6900 | ጥር 19፣ 2022 (ስፓኒሽ) 7:00 ፒ.ኤም<br>ጥር 20፣ 2022 (እንግሊዘኛ) 7:00 ፒ.ኤም |
| **ጄፈርሰን**<br>703-228-5900 | ጥር 7፣ 2022<br>7:00 ፒ.ኤም |
| **ኬንሞር**<br>703-228-6800 | ጥር 5፣ 2022 (ስፓኒሽ) 7:00 ፒ.ኤም<br>ጥር 12፣ 2022 (እንግሊዘኛ) 7:00 ፒ.ኤም |
| **ስዋንሰን**<br>703-228-5500 | ጥር 13፣ 2022<br>6:30 ፒ.ኤም |
| **ዊሊያምስበርግ**<br>703-228-5450 | ጥር 12፣ 2022<br>7:00 ፒ.ኤም |
| **H-B ዉድልዋን**<br>703-228-6363 | ጥር 11፣ 2022<br>7:00 ፒ.ኤም |

# APS መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

## ዶሮቲ ሃም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

**ኤለን ስሚዝ፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-2910
dorothyhamm.apsva.us
4100 Vacation Lane, Arlington, Virginia 22207



በቼሪዴል ኮሚውኒቲየሚገኘው ዶሪቲ ሃም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1994 ጀምሮ የተከፈተ የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤት አጎራባች መካከለኛ ትምህርት ቤት ነው። ዋናው ህንጻ በ1951 ሲጠናቀቅ፣ ለዶሪቲ ሃም ሰፊ የመተላለፊያ መንገዶችን፣ ብሩህ ክፍሎችን፣ እና የሚያማምሩ የቴራዞ ወለሎችን አቅርቧል፣ የውስጠኛው ክፍል ደግሞ አዲስ ሎከሮችን፣ ቀለም ያለውን ግድግዳ፣ እና ለስነጥበብ፣ ለቢዝነስ ትምህርት፣ ለቴክኖሎጂ ትምህርት፣ እና ለቤተሰብ እና ለሸማቾች ሳይንስ የፈጠራ መማሪያ ክፍል የሚሆኑ ክፍሎችን ለማካተት ተሻሽሏል። በህንጻው ምEራባዊ ክፍል ላይ የተጨመረው ክፍል ረዳት ጂም፣ የጤና/የአካል ብቃት መስሪያ ቦታ፣ የሎከር ክፍሎች፣ የሚያምር ቤተ መጽሃፍት፣ የተማሪ መደበኛ ቦታ ከ ሚዲያ ግድግዳ ጋር፣ እና 3 የዘመናዊ ሳይንስ የመማሪያ ክፍሎችን ጨምሮ 15 ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችን ያካትታል። በተጨመረው ክፍል አካባቢ ያለው የመሬት አቀማመጥ በ1959 ዋናውን Stratford Jr. High ህንጻን ስለሰሩ አራት ተማሪዎች ለተማሪዎች እና ለማህበረሰብ አባላት የሚያከብር እና የሚያስተምር የመንገድ መተላለፊያን ያካትታል።

በሆልስ ሂል ሬዚደንት፣ እናት እና የአርሊንግተን የሰብአዊ መብቶች አክቲቪስት በሆኑት በ ዶሮቲ ኤም. ቢገሎው ስም የተሰየመው፣ የዚህ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰራተኛ ሁሉም ተማሪዎች ጥንቃቄ የተሞላበት፣ ጠቃሚ በሆነ እና የተደራጀ ቋንቋ ባለው የትምህርት ተሞክሮ በእኩልነት ተደራሽነት እንዲኖራቸው ቀጣይነት ያለው ስራ እየሰሩ ነው። የተማሪ ተኮር የማስተማር ልምምዶችን በመጠቀም ተማሪዎችን የግል የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት የመማሪያ ክፍልን፣ የተማሪ ድምጽን ግምት ውስጥ ማስገባትን፣ በጣቢያዎች እና በዎርክሾፖች ትክክለኛ የመማሪያ ልምዶችን መፍጠርን፣ አስተማሪዎች የ APS የስርዐተ ትምህርትን መለየትን ያዋህዳሉ።

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ስትራቴጂክ እቅድ፣ ከጉርምስና እድሜ ላይ ከሚገኙ ጥናቶች ጋር፣ በትምህርት ቤት ከአንድ አዋቂ ጋር ያለው አዎንታዊ ግንኙነት ለስኬት ቁልፍ ሊሆን እንደሚችል ይገለጻል። በዶሮቲ ሃም፣ TA (የማማከር አስተማሪ) አስተማሪ የልጁ የመጀመሪያ ጠበቃ ነው። ተማሪዎችን በደስታ ይቀበላሉ፣ ተማሪዎች የባለቤትነት ስሜትን እንዲያዳብሩ፣ የተማሪ አደረጃጀት ክህሎቶችን ያመቻቻሉ፣ እናም የተማሪዎችን አካዳሚክ አፈጻጸም በመከታተል ይደግፋሉ። ከዚህ መምህር ጋር የወላጅ አጋርነት የትምህርት ቤቱን የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት አመታትን ለእያንዳንዱ ተማሪ “ምርጥ አመታት” የማድረግ ተልዕኮ የሚጠቅም ነው።

## ገንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*ካውንቲ አቀፍ ስፓኒሽ ከፊል-መግቢያ ፕሮግራም እና ሞንቴሶሪ መካከለኛ አመታት ፕሮግራም*

**ዶክተር ሎሪ ዊጊንስ፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-6900; 703-519-9183 (ፋክስ)
gunston.apsva.us
2700 South Lang Street, Arlington, Virginia 22206

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



የገንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዩናይትድ ኔሽንስን-የሚመስልየተለየ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ገንስተን ሶስት የተለያዩ ነገር ግን እርስ በርስ የተያያዙ ፕሮግራሞች፣ ከፊል ስፓኒሽ- መግቢያ ፕሮግራም፣ ሞንቴሶሪ የመካከለኛ አመታት ፕሮግራም፣ እና የባህላዊ መካከለኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም መገኛ ነው። በተጨማሪም፣ በጣም በተለያየ የተማሪ አካል ውስጥ ከ50 በላይ የሆኑ የተለያዩ ሃገራት ተወክለዋል።

የሚጠበቀው ሁሉም የገንስተን ተማሪ ለሁለተኛ ደረጃ እና ከዚያ በኋላም በርካታ አማራጮችን ለማግኘት ያሉትን ጠንካራ የኮርስ ስራዎች ይሞክራሉ ተብሎ ነው። ግቡ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ እና ከዚያ በኋላም ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ችሎታ እና ተሰጥዖ ይዘው እንዲወጡ ነው። የገንስተን ሰራተኞች ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር – ከእያንዳንዱ ተማሪ፣ ከእያንዳንዱ ወላጅ፣ እና ከእያንዳንዱ መምህራን አባል ጋር – እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትብብር እና መከባበርን እና ግንዛቤን በሚያሳድግ ሁኔታ ውስጥ ይሰራሉ።

ከባድ ከሆነ የአካዳሚክ ፕሮግራም በተጨማሪ፣ ገንስተን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በርካታ ከመደበኛ ውጪ እና ከስርዐተ ትምህርት ውጪ የሆኑ ተግባራት እና የእነርሱን ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አዕምሯዊ እድገት የሚመርጡውን ያንን ድጋፍ አሏቸው። ተማሪዎች ከትምህርት ጋር በሚገናኝ አትሌቲክስ ላይ የመሳተፍ ምርጫ እና ከ25 በላይ የሆኑ የተለያዩ ክበቦች እና ከትምህርት በኋላ የሚካሄዱ ተግባራት ምርጫ አላቸው። በተጨማሪም፣ የገንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከትምህርት በኋላ ባለ የወጣቶች መዝናኛ ፕሮግራም ፖንሰር ከሚደረግለት ከአርሊንግስተን ካውንቲ የፓርኮች እና መዝናኛ መምሪያ ጋር በአጋርነት የሚሰራ የጋራ መጠቀሚያ ተቋም ነው።

እንዲሁም ገንስተን ሽልማትን ያስገኙ ዘመናዊ ስነTበቦDች እና የቴክኖሎጂ ፕሮግራም አሉት። በስነ ጥበብ፣ በድራማ፣ በሙዚቃ፣ እና በቪዲዮ ጋዜጠኝነት ላይ የተሳተፉት ተማሪዎች ለትጋታቸው እና ለተሰጥኦዋቸው በአካባቢ እና በስቴት አቀፍ ውድድሮች በቋሚነት ክብር ይሰጣቸዋል። በአስተማሪዎች መካከል ያለው ትብብር ለልዩ እና ለፈጠራ ትምህርት ልምዶች ከተመረጡ አማራጮች ጋር ተማሪዎች የኮርስ ስራውን ይዘት እንዲረዱት ብዙ እድሎችን ይፈጥራል።

በገንስተን ውስጥ የሚገኙ የላቁ ሰራተኞች በአካዳሚክ ተግዳሮት ለሚያጋጥማቸው እና እውቀትን ለማግኘት ለሚጥሩ ተማሪዎች የትምህርት እድሎችን ለመፍጠር እየሰሩ ነው። በቤት እና በትምህርት ቤት መካከል ባለው የትብብር መንፈስ ተማሪዎች ይጠቀማሉ፣ ይህም ገንስተንን ሁሉም ልጆች ስኬታማ የሚሆኑበት ቦታ እንዲሆን ያደርገዋል። በገስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ተልዕኮ፡ ስኬት!

## H-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም

*የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራም*

**ዶክተር ኬሲ ሮቢንሰን፣ ርዕሰ መምህር**

703-228-6363; 703-558-0317 ፋክስ)
[hbwoodlawn.apsva.us](hbwoodlawn.apsva.us)
1601 Wilson Blvd., Arlington, Virginia 22201



የH-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም በአራት ምሰሶዎች ላይ ያከብራል:- ተንከባካቢ ማህበረሰብ፣ በራስ አስተዳደር፣ ፍትሃዊነት እና በራስ የመመራት ትምህርት። እያንዳንዱ ተማሪ፣ አስተማሪ እና ወላጅ እኩል ድምጽ በሚያገኝበት፣ በተማሪዎች መር የተማሪ መር ተመራጮች እና ክበቦች፣ እና በሳምንታዊ የከተማ ስብሰባዎች በኩል፣ ማህበሰረቡ ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ግቦቻቸውን እንዲያሳድጉ እና እንዲያሳኩ እንዲሁም የቤተሰብነት ስሜት እንዲሰማቸው በጋራ ይሰራል።

የተማሪ ምርጫ የ H-B ዉድላውን አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም ዋና ትኩረት ነው። ተማሪዎች ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት ሰአታቸውን እንዴት በጥበብ መጠቀም እንዳለባቸው መወሰን አለባቸው። በራስ የመመራት ጊዜ ከ6ኛ ወደ 12ኛ ክፍል ቀስ በቀስ ይጨምራል። ይህን የነጻነት ስራ ለመስራት፣ ትምህርት ቤቱ በተማሪዎቹ መልካም ፍላጎት ያምናል፣ እናም የግል ሃላፊነት እሴትን ያስተምራል። በ1971፣ "ለአዋቂ ሰው አንድ ቃል በቂ ነው" የሚለው መሪ ቃል ነጻነት ከሃላፊነት ጋር ያለውን ትስስር ለማንጸባረቅ እንደ መሪ ቃል ተመርጧል።

እያንዳንዱ ተማሪ ወደ H-B ውድላውን ፕሮግራም የሚገባው በተለያየ ራስን የመቻል እና የራስ ተነሳሽነት ደረጃ ነው። መምህራን ተማሪዎች እንደ ግለሰብ፣ በትምህርታዊ ፕሮግራሞቻቸው ላይ ቁጥጥር እንዲኖራቸው ለማድረግ ከተማሪዎች ጋር እንደ አነስተኛ ቡድኖች እና እንደ ክፍል ደረጃዎች ይሰራል። እንዲሁም H-B ዉድላውን በአስተማሪ የማማከር ፕሮግራም በኩል የተማሪዎችን ፍላጎቶች ያሟላል TA ፕሮግራም እያንዳንዱ ተማሪ በህንጻው ውስጥ ከአዋቂ ጋር መገናኘቱን እና ሁሉም ቤተሰብ የተሰጠ የግንኙነት ነጥብ እንዳላቸው ያረጋግጣል። አስተማሪዎች እና TAዎች እያንዳንዱ ተማሪ የአካዳሚክ እና የማህበራዊ አቅም ግባቸውን ለመድረስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ በጋራ ይሰራሉ።

ተልዕኳችን ለ H-B ውድልዋን ተመራቂዎች አባላቶቹን የሚያደንቅ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ በአዋቂ ሰው እንዲቀርቡ የሚያዘጋጅ፣ ስለ ፍላጎቶቻቸው እና ችሎታዎቻቸው ትክክለኛ ግንዛቤ፣ ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ማህበረሰብ ውስጥ መሆን እና መማር ነው።

## ቶማስ ጄፈርሰን ትምህርት ቤት

*አለም አቀፍ ባካሉሬት መካከለኛ አመታት ፕሮግራም አለም ትምህርት ቤት*

**ኬሻ ቦጋን፣ ርዕሰ መምህር**

703-228-5900; 703-979-3744 (ፋክስ)
[jefferson.apsva.us](jefferson.apsva.us)
125 South Old Glebe Road, Arlington, Virginia 22204

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



የቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት በ2007 የጸደይ ወቅት በአለም አቀፍ ባካሎሬት ድርጅት (IBO) ፈቃድ ያገኘ የአለም አቀፍ ባካሎሬት መካከለኛን አመት ፕሮግራም (IBMYP) ነው።

ፕሮግራሙ ተማሪዎችን የሁለገብ ትምህርት እና አስተያየት አስተሳሰብን በሚያበረታታ የስነ ምግባር አቀራረብ የአለማቀፍ አካዳሚክ ፕሮግራም ተጋላጭ እንዲሆኑ ለማድረግ የተነደፈ ነው። እንደ አርሊንግስተን ብቸኛው የIB መካከለኛ አመት ፕሮግራም፣ ከእድሜ ልጅ የመማር ክህሎት በተጨማሪ ለተማሪዎች የአካዳሚክ ፈተና ማዕቀፍን ያቀርባል። ይህ ፕሮግራም "ባህላዊ የትምህርት ቤት የትምህርት አይነቶችን የሚይዝ፣ ነገር ግን የሚያልፍ ትምህርታዊ አቀራረብን ያቀርባል።"

ተማሪዎች በማህበረሰብ ፕሮጀክቶች እና በአገልግሎት ተግባራት፤ የማህበረሰብ ፕሮጀክት ማሳያ፣ አለምአቀፍ ፌስቲቫል፤ የሳይንስ ማሳያ እና አለም አቀፍ የፊልም ቀን ላይ ይሳተፋሉ። ቶማስ ጄፈርሰን እንደ ምርጫ በስድስተኛ ክፍል መጀመሪያ ላይ የፊት-ለ-ፊት አለም ቋንቋዎች መመሪያን ያቀርባል። የቶማስ ጄፈርሰን ተማሪዎች የተማሪ-መሪ ኮንፍረንስን ያካሂዳሉ በዚህም ተማሪዎች ከወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው እና ከአካዳሚክ አማካሪዎቻቸው ጋር ውይይቱን ይመራሉ።

በ2019፣ የቶማስ ጄፈርሰን ተማሪዎች ለስራቸው እና ለትጋታቸው በአካባቢ ውስጥ እና በሃገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ተሰጥቷቸዋል። የእንደዚህ አይነት እውቅና ምሳሌዎች በትምህርት ቤቶች NEXT Design ላይ ውድድር አንደኛ ቦታ ማግኘትን፤ በAPS HEADS UP አንደኛ ደረጃን መያዝን ያካትታሉ! PPSA ውድድር፤ IBን መቀበል
የማዕከላዊ-አትላንቲክ የምርጥ አስተማሪ ሽልማት፤ እና በፈተና መዝገብ ቁጥሮች ክሬዲት ማግኘት። የቶማስ ጄፈርሰን ተማሪዎችን እንዲሁተሳትፈዋል እናም በNOVA ክልላዊ ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ እናም የሞዴል ዩናይትድ ኔሽንስ ኮንፍረንስ ላይ ተቀምጠዋል፣ እናም በ2018 ካውንቲ ውድድር ላይ አሸናፊዎች ነበሩ።

ቶማስ ጄፈርሰን ለማያቋርጥ ትምህርት ተማሪ ላይ ትኩረት ያደረገ አቀራረብን ያቀርባል። የስነምግባር ቡድን ተለዋዋጭ መርሃግብር እና የአስተማሪ-አማካሪ ፕሮግራም የትምህርት ቤቱ ፕሮግራም ዋና አካል ናቸው። በቶማስ ጄፈርሰን ያሉ ሰራተኞች ሁሉም ተማሪዎች የሚያድጉበት እና ከፍተኛ የሚባል ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚፈተኑበትን አስደሳች እና ውጤታማ የሆነ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ለመፍጠር ያለማቋረጥ ይሰራሉ። በቶማስ ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ *ራሳችንን፣ ወደፊታችንን፣ እና አለማችንን ለመረዳት እና ለማሻሻል በጋራ በመማር እናምናለን።*

## ኬንሞር መካከለኛ ትምህርት ቤት

በ *STEAM* የተጎላበተ
የስነ ጥበብ እና ግንኙነቶች ቴክኖሎጂ ትኩረት

**ዴቪድ ማክብራይድ፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-6800; 703-998-3069 (ፋክስ)
[kenmore.apsva.us](kenmore.apsva.us)
200 South Carlin Springs Road, Arlington, Virginia 22204

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



ኬንሞር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በSTEAM (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ጥበብ እና ሂሳብ) የተሰራ በጥበብ እና በቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ያደረገ ትምህርት ቤት ነው። የአካዳሚክ ስርዐተ ትምህርቱ የሚበለጽገው በተሻሻለ ተማሪዎች ስነጥበብን እና ቴክኖሎጂን ከትምህርት ጋር በሚያዋህዱ በተጋሩ ስራዎች ላይ በሚሰሩበት የመማር ፈጠራ ዘዴዎች ነው። ኬንሞር አመቱን ሙሉ ትኩረቱን በሙዚቃ፣ በድራማ እና በውዝዋዜ እንዲሁም አመታዊ የቡና ቤት፣ ስነጥበብ እና የጃዝ ማሳያ፣ የሳይንስ ምሽት፣ እና የትኩረት ፌስቲቫልን ያከብራል።

የኬንሞር ተማሪዎች በሃገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ስነጥበብ ሽልማቶችን አሸንፈዋል፤ ለቨርጂኒያ የሳይንስ አካዳሚ የሳይንስ ምርምር ወረቀቶችን አቅርበዋል፤ በቃል ውድድር እና በብሄራዊ የላቲም ፈተና ውድድር መወዳደር፤ ለባንዶች፣ ለኳየርም እና ለኦርኬስትራ በሙዚቃ ፌስቲቫሎች ላይ፣ ከፍተኛ ክብርን አግኝተዋል፤ እና ብዙ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን አጠናቅቀዋል።

የኬንሞር ትኩረት ባለፉት 25 አመታት ውስጥ ተሻሽሏል አሁን ደግሞ የSTEAM ማረጋገጫ ተማሪዎች ከSTEAM ጋር የተገናኙ ርዕሶችን እና ልምዶችን ከመደበኛ ትምህርት ውጪ እንቅስቃሴዎች እንደ First Robotics፣ Kenmore Cougar News፣ እና ACT II ትምህርቶች ያበረታታል።

ኬንሞር ቤተሰቦች የሚሳተፉበት እና የሚያከብሩት ሁሉን ያካተተ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ነው። የወላጅ ወርክሾፕ እና የድጋፍ ቡድኖች በትምህርት ቤቱ ኬንሞር PTA እና ከትምህርት ቤት ክፍል ጋር በመተባበር ይስተናገዳሉ። የማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት በማህበረሰብ አገልግሎት እና በጎ ፈቃደኝነት ውስጥ ተካትቷል።

ትምህርት ቤቱ(PBIS)ን ለማስተዋወቅ አዎንታዊ የባህሪ ስልታዊ አቀራረብን ይጠቀማል። የአካዳሚክ ጣልቃገብነት በተለዋዋጭ የአስተማሪ የምክር ቡድኖች፣ እንዲሁም በተመራጮች እና ከትምህርት-በኋላ በሚደረግ ድጋፍ ይደገፋል።

የኬንሞር ተቋም እንደ የመኸር ህልሞች፡ የሂስፓኒክ ባህል አከባበር፣ በልዩ ፕሮግራሞች ውስጥ ላሉ ተማሪዎች የInclusion Revolution pep rally፣ እና አመታዊ አፍሪካዊ-አሜሪካዊ ንባብ ያሉ ልዩነትን እና ማካተትን የሚያከብሩ በርካታ የትምህርት ቤት እና የዲስትሪክት ፕሮግራሞችን ያስተናግዳል።

ህንጻው በ2017 እድሳት ተደርጎበታል ይህም አሁን ያለውን የዲዛይን አስተሳሰብ እና ሮቦቲክስ አዲስ የፈጠራ ላቦራቶሪን፣ የተራዘሙ የመማሪያ ክፍሎችን፣ የተስተካከለ ብዙ ጥቅም ያለውን ክፍል፣ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ክፍሎች ተጨማሪ ቦታን፣ እና የማህበረሰብ ክበብ ክፍልን ያካትታል።

## ስዋንሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*የትምህርት ቦርድ ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ሽልማት፣ 2020*
*የአስተዳደር የእውቀት ትምህርት ሽልማት፣ 2018*
*የትምህርት ልቀት ሽልማት ቦርድ፣ 2016, 2018*
*የትምህርት ስኬት ቦርድ ሽልማት፣ 2014፣ 2017፣ 2019*

**ሬኔ ሃርበር፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-5500; 703-536-2775 (ፋክስ)
[swanson.apsva.us](swanson.apsva.us)
5800 N. Washington Blvd., Arlington, Virginia 22205

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*




ስዋንሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲማሩ እና ሲያድጉ የመደገፍ የረጅም ጊዜ ባህልን በማስቀጠል የነጻ የትምህርት እድል ~መንፈስ~ አገልግሎት መሪ ቃላችንን በማሳየት 82ኛ አመቱን በጥር 2021 አክብሯል።

የትምህርት ቤታችን ማህበረሰብ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጅን አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና አዕምሯዊ እድገት ፍላጎቶችን ለማሟላት በትጋት ይሰራል። የማስተማሪያ ሰራተኞቻችን ከስፖርት እስከ ሮቦቲክስ የሚሆኑ ተግባራትን ያካተተ የሁለገብ ቡድን ማስተማርን፣ ተለዋዋጭ መርሃግብር፣ የአስተማሪ የምክር ፕሮግራም (STAR)፣ የፈላጊ ኮርስ አማራጮችን እና ሰፊ ከመደበኛ ትምህርት ውጪ የሆኑ ፕሮግራምን በማክበር ያስተዋውቃሉ። ስዋንሰን የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ግቦች በጥንቃቄ ምት ውስጥ በማስገባት መመሪያን ያቀርባል እንዲሁም የተማሪዎቻችንን የባህል ልዩነት ያከብራል። የመማር እድሎች ተማሪዎች እንዴት መረጃን እንደሚተነትኑ እና እንደሚረዱ፣ ችግሮችን እንደሚፈቱ፣ ከለውጥ ጋር እንደሚላመዱ እና የእድሜ ልክ ተማሪዎች እንደሚሆኑ የአለም ማህበረሰብ ፍሬያማ አባላት እንዲሆኑ ያሳትፋል።

እንደ ብቁ የመማሪያ ማህበረሰብ፣ የስዋንሰን አስተማሪዎች ተማሪዎች የሚያውቁትን ነገር ላይ ለማሳደግ እና የተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት በግለሰብ ደረጃ በየሳምንቱ እርስ በርስ በመተባበር ይሰራሉ።

የስዋንሰን አስተማሪዎች እና ሰራተኞች ሙያዊ ተግባራቸውን ለማሻሻል፣ ተግባራት ለመምራት፣ የተማሪዎችን የእውቀት ፍላጎት የሚያበረታታ እና የሚያስቡ ተማሪዎችን ለማፍራት በተዘጋጀ ትርጉም ባለው ሙያዊ እድገት ላይ ተማሪዎችን በሚያሳትፉ ተግባራት ላይ በቋሚነት ለመሳተፍ ይሰራሉ።

ስዋንሰን የተማሪዎቹን አጠቃላይ የአካዳሚክ እና ማህበራዊ ስኬት ለማረጋገጥ ከወላጆቻችን ጋር ያለውን አጋርነት ያከብራል። በ ስዋንሰን፣ ስኬት የማህበረሰብ ጥረት ሲሆን ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ እና ሰራተኞችን ያካትታል። የስዋንሰን አስተዳዳሪዎች ነን!

## ዊሊያምስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

*የአስተዳዳሪው የእውቀት ትምህርት ሽልማት፣ 201፣, 2017*

*የእውቀት ትምህርት ሽልማት ቦርድ፣ 2014፣ 2018፣ 2019*

**ብሪያን ቦይኪን፣ ርዕሰ መምህር**
703-228-5450; 703-536-2870 (ፋክስ)
williamsburg.apsva.us
3600 North Harrison Street, Arlington, Virginia 22207

*ይህ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ እውቅና ተሰጥቶታል።*



በ1955 የተጀመረው የዊሊያምስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤትበአርሊንግተን ውስጥ ባለው ጠንካራ የትምህርት ወሳኙ አካል ነው። የተሰየመው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ባሉት ታሪካዊ ከተማዎች በአንዱ ሲሆን፣ ትምህርት ቤቱ የበፊቱን ጥሩ ነገር በመጠበቅ እና ተማሪዎችን ወደፊት በመምራት ይህን ጠንካራ ታሪክ ለመጠበቅ በትጋት ይሰራል።

የትምህርት ቤታችን ማህበረሰብ የሁሉንም እኩልነት፣ ተደራሽነት፣ እና ከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች ያከብራል። በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መካከል ያለው ሽግግር ስኬታማ እንዲሆን መምህራን ከሰራተኞች ጋር በጋራ ይሰራሉ። ዊሊያምስበርግ ብዝሃነትን በማክበር፣
የባህሪ ትምህርትን በመተግበር፣ እና የ21ኛ ክፍለዘመን ቴክኖሎጂን ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያዘጋጃል።

የዊሊያምስበርግ አካዳሚክ ፕሮግራም የክፍል ደረጃ ተማሪዎች በአካዳሚክ፣ በማህበራዊ እና በስሜታዊ ደረጃ የሚያድጉበትን የውስጥ ስነምግባር ቡድን የመማር አቀራረብን ያካትታል።
የትምህርት ቤቱ የአካዳሚክ ስኬት የሚለየው ለተለየ ትምህርት፣ ለግል በተዘጋጀ ትምህርት፣ እና በተማሪ ላይ
ያተኮረ ሙያዊ ትምህርት ማህበረሰብ ባለን ቁርጠኝነት ነው። አስተማሪዎች፣ አማካሪዎች እና አስተዳዳሪዎች፣ ተማሪዎች የግል ጥቅሞቻቸውን በመመርመር አሳቢ፣ ፍሬያማ እና የማህበረሰቡ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ አባላት እንዲሆኑ እድል የሚሰጣቸውን የትምህርት ልምዶች ለማቅረብ በጋራ ይሰራሉ።

ከትምህርት-በኋላ ያለው ሰፊ ፕሮግራም የተማሪዎችን ፍላጎቶች እና የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ያንጸባርቃል። ተግባራቶች የአካዳሚክ ብልጽግናን፣ ሮቦቲክስን፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን፣ እና ሌላ በተማሪ የሚመሩ ክበቦችን ያካትታሉ። እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ሰፊ የውስጥ እና ከትምህርት ጋር የሚገናኙ ስፖርቶችን ያቀርባል። ከ አትሌቲክስ በተጨማሪ፣ WMS ተማሪዎቻችን በአካባቢያዊ እና በስቴት ደረጃዎች ለላቀ ስኬት
በዘላቂነት እውቅና የሚያገኙበት የላቀ ጥበብ ፕሮግራም አለው።

ዊሊያምስበርግ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ደጋፊ በሆነ አካባቢ ውስጥ፣ ማህበረሰባቸውን የሚረዱ እና ባህላቸውን የሚያከብሩ ተማሪዎችን ለማሳደግ በትጋት ይሰራል።

# ተማሪዎን ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመዝገብ

## የአሁኑ ጊዜ የአርሊንግተን ተማሪዎች

### የኮርሶች ምርጫ/የአካዳሚክ እቅድ ማውጣት

አንደኛ ደረጃ ወደ መአከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግርን ቀላል ለማድረግ፣ የመካከለኛ ደረጃ አማካሪዎች በመጋቢት መጨረሻ እና በየካቲት መጀመሪያ ላይ ከአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ለመገናኘት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይጎበኛሉ። የወላጆች የመረጃ ክፍለጊዜዎች ወላጆችን በአካዳሚክ እቅድ ማውጣት እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶችን እንዲረዱ ያግዟቸዋል። የ2022-23 - የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ጥናቶች (POS)፣ የካቲት ላይ የሚደረግ ሲሆን፣ በስርዐተ ትምህርት ውስT ስለሚሰTኡ እና በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ ስለሚሰጡ አገልግልቶች አጠቃላይ እና የተብራራ መረጃ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ለስድስተኛ ክፍል ኮርሶችን ለመምረጥከመማሪያ ክፍል አስተማሪያቸው፣ ከትምህርት ቤት አማካሪያቸው አር እና ከወላጆቻቸው ጋር ይሰራሉ። የኮርስ መጠየቂያው ቅጽ (CRF) በወላጅ ተሞልቶ እና ፈቃድ አግኝቶ ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይላካል። ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ የትምህርት ደረጃ ከ4-6 አመት አካዳሚክ እቅድ ያዘጋጃሉ ይህም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይከተላቸዋል። የእያንዳንዱ ተማሪ እቅድ በግለሰብ ደረጃ ሲሆን ተማሪውን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማዘጋጀት ከፍተኛ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ መንገድ ይከፍትላቸዋል። እቅዱ ከትምህርት ቤት አማካሪው ጋር ስብሰባ በሚደረግበት ወቅት በየአመቱ በተማሪው ይሻሻላል። ወላጆች እንዲሳተፉ በደንብ ይበረታታሉ። ስለ አካዳሚክ እቅድ ማውጣት ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ apsva.us/academicplanningን ይጎብኙ።

## አዲስ ተማሪዎች

የልጅዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋው/ቋንቋዋ ከእንግሊኛ ቋንቋ ሌላ ከሆነ፣ ወይም የትምህርት ስርዐትን ከሃገር ውጪ ሲከታተል ከነበረ፣ የቋንቋ አገልግሎት ምዝገባ ማዕከልን (LSRC) በ703-228- 7663 በማነጋገር ልጅዎን ያስመዝግቡ። በሌሎች በሁሉም ጉዳዮች፣ ልጅዎን በአካባቢዎ ባለ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም ልጅዎ ተቀባይነት ያገኘበት ትምህርት ቤት ያስመዝግቡ። ተጨማሪ መረጃ apsva.us/ lsrc/student-registration/ላይ ይገኛል።

### ልጅዎን ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- የልጁ እድሜ እና ህጋዊ ስም ማረጋገጫ-የተረጋገጠ የልደት የምስክርነት ወረቀት ግልባጭ (የተረጋገጠው ግልባጭ መቅረብ ካልቻለ፣ የምስክርነት ቃል መሞላት አለበት። APS የዚህን የምስክርነት ቃል ግልባጭ ለህግ አስፈጻሚ ኤጀንሲ የማስተላለፍ መብት አለው)።
- የተማሪው ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት አርሊንግተን ውስጥ እንደሚኖሩ ማረጋገጫ፡ ወቅታዊ የኪራይ ውል ወይም የሞርጌጅ ስምምነት
- የሚመለከተው እና የሚገኝ ከሆነ፣ ከሌላ የትምህርት ቤት ስርዐት ወይም ሃገር ይፋዊ የትምህርት ቤት መዝገቦች
- የተማሪው የምዝገባ ቅጽ፣ ተሞልቷል እና ለትምህርት ቤቱ ቀርቧል። ይህ ቅጽ በማንኛውም የአርሊንግተን ትምህርት ቤት ወይም በ apsva.us/registration ይገኛል።
- ከመግባቱ አስቀድሞ በ12 ወራት ውስጥ የተደረገ የሳንባ ነቀርሳ ማጣሪያ ክትባት መዝገቦች እና ሰነዶችን ያካተተ የህክምና መረጃ (የጤና መስፈርቶችን ይመልከቱ)

ለተጨማሪ መረጃ እና ለመመዝገቢያ ለሚያስፈልጉ ለሁሉም ቅጾች፣ ወደ ድረገጽ "የምዝገባ" ክፍል ወደ APS ድህረ ገጽ www.apsva.us.

### የጤና መስፈርቶች

***ማሳሰቢያ፡ ተማሪ(ዎች) ያለእነዚህ መስፈርቶች ትምህርት መጀመር አይፈቀድለትም።***

#### አካላዊ ምርመራ

የተማሪው የህክምና መረጃ (ክትባቶች እና የአካል ምርመራ፣ ካለ) ለትምህርት ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል። ከትምህርት ቤት መግቢያ 12 ወራት በፊት የአካል ምርመራ ቢደረግ ይመከራል፣ ነገር ግን ተማሪው በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስፖርቶች ላይ የሚሳተፍ ካልሆነ አስፈላጊ አይደለም። የክትባት መዝገብ ያስፈልጋል እና የእያንዳንዱን ክትባት ወር፣ ቀን እና አመት መዘርዘር አለበት። *ስለሚፈለጉ ክትባቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከዚህ በታች ይመልከቱ።*

#### የሳንባ ነቀርሳ መስፈርቶች

ትምህርት ከመጀመሩ ከ12 ወራት አስቀድሞ የተደረገ የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ማጣሪያ ሰነድ ያስፈልጋል። የቲቢ ማጣሪያ እና/ምርመራ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም በU.S ተቋም መሰራት አለበት እናም ፈቃድ ባለው የህክምና ባለሙያ (ማለትም፣ ሀኪም፣ ነርስ ሀኪም፣ የተመዘገበ ነርስ ወይም የሀኪም ረዳት) መረጋገጥ እና መፈረም አለበት። ማጣሪያው የበሽታ ምልክቶችን ግምገማ፣ የስጋት ምዘና፣ እና ከተለየ የቲቢ የቆዳ ምርመራ ወይም ቲቢ የደም ምርመራ (በተለምዶ "IGRA" በመባል የሚታወቅ) ማካተት አለበት።

#### የሚያስፈልጉ ክትባቶች

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ወቅቱን የጠበቀ የክትባት መዝገብ ማቅረብ አለባቸው።

በተጨማሪም፣ የሚመዘገቡ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚከተሉት ያስፈልጓቸዋል፡

- ቲታነስ/ዲፍቴሪያ/ፐርቱሲስ (Tdap)
- ማኒንንኮካል (MenACWY)
- የ HPV ክትባት (የመጀመሪያው መጠን የሚሰጠው 7ኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ነው። ወላጆች ክትባቱን ባለመውሰድ የ HPV መስፈርትን "መዝለል" ይችላሉ። ምንም የ"መዝለል" ሁኔታ ደብዳቤ ወይም ማረጋገጫ አያስፈልግም።)

ለትምህርት ቤት መግቢያ ለአነስተኛ የክትባት መስፈርቶች ዝርዝር መረጃ፣ ወደ www.vdh.virginia. gov/immunization/requirements/ ይሂዱ።

ስለጤና መግቢያ መስፈርቶች ወይም ክትባቶች ጥያቄዎች በህዝብ ጤና ነርስ ወይም በእያንዳንዱ የአርሊንግተን ትምህርት ቤት የትምህርት ቤት የጤና እርዳታ ወይም በትምህርት ቤት ጤና ቢሮ በ703-228-1651 ሊመለሱ ይችላሉ።

### በስፖርቶች መሳተፍ

ትምህርት ቤት ሲዘጋ ስፖርት ላይ ለመሳተፍ፣ ተማሪው በግንቦት 1 ወይም ከዛ በኋላ የተሞላ የአካል ምርመራ ቅጽ ሊኖረው ይገባል። ቅጾች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም በ www.vhsl.org/forms/ይገኛሉ። የተሞሉ ቅጾች ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት የእንቅስቃሴ ዳይሬክተር መመለስ አለባቸው።

# የመግቢያ ፕሮግራም ምዝገባ መረጃ

### መግቢያ ምንድነው?

መግቢያ በየቀኑ ከትምህርት በኋላ የሚደረግ ፕሮግራም ሲሆን ለተመዘገቡ የስድተኛ፣ ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚቆጣጠሩ፣ የንብረት-መገንበት ተግባራትን ያቀርባል። ይህ ፕሮግራም የሚካሄደው በአምስቱም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መደበኛ የትምህርት ሰአት መውጫ እስከ ምሽቱ 6 ሰአት ባሉ በሁሉም የትምህርት ቀናት ነው።

መግቢያ ተማሪዎች የሚያጠኑበትን፣ የሚዝናኑበትን ወይም በተለያዩ ተግባራት ላይ የሚሳተፉበትን በጎ አካባቢ ያቀርባል። እንዲሁም ተማሪዎች በማናቸውም በትምህርት ቤቱ በመደበኛነት በሚደረጉ እንደ የውስጥ ፕሮግራሞች እና ክበቦች ያሉ ከትምህርት-በኋላ የሚደረግ ተግባራት ላይ መሳተፍ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ መግቢያ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ተግባር ከሚሄዳቸው በፊት በፕሮግራሙ ተቆጣጣሪ እንዲወጡ እና ሲመለሱ እንዲገቡ ይጠይቃል።

የተማሪዎች የፕሮግራም ምዝገባ ወርሃዊ ክፍያ በተለያየ መለኪያ ሲሆን፣ በቤተሰቡ ገቢ ይወሰናል።

### የምዝገባ ሂደት

ምዝገባ የሚጀምረው በ2022 ጸደይ ወቅት በኦንላይን በapsva.us/extdayነው። የኮምፒውተር ተደራሽነት እና የምዝገባ እርዳታ በተራዘመ ቀን ማዕከል ቢሮ ይገኛሉ።

ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎ የተራዘመ ቀን ማዕከል ቢሮን፣ በ extended.day@apsva.us ወይም በ703-228-6069 ያግኙ። የተራዘመ ቀን ማዕከል ቢሮ የሚገኘው በሲፋክስ የትምህርት ማዕከል፣ 2110 Washington Blvd., Arlington, VA 22204 ነው።

## ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች ጠቃሚ ምክሮች

ቀጣዮቹ ሶስት አመታት ለልጅዎ የአካዳሚክ እድገት እና ግኝት፣ ራስን በመቻል የማደግ፣ እና የአካላዊ እና የስሜታዊ ለውጦች ጊዜያት ናቸው። በልጅዎ ህይወት ውስጥ በጣም ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰው እንደሆኑ እንዲቀጥሉ ለማረጋገጥ፣ ለሚከተሉት ነገሮች ቆራጥ ይሁኑ፡

- በትምህርት ቤት እና በስርዐተ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፉ።
- በልጅዎ ትምህርቶች ላይ ፍላጎት ያሳዩ እና ልጅዎ የቤት ስራ መስሪያ ሰአቱን እንዲያዘጋጅ ያግዙት።
- የትምህርት ቤቱን አማካሪዎች እና አስተማሪዎች በየጊዜው ያነጋግሩ እና በወላጅ-አስተማሪ ኮንፍረንሶች ላይ ይገኙ።
- ተማሪዎ በመደበኛነት ትምህርት ቤት መሄዱን ያረጋግጡ።
- ተማሪዎ አዲስ ፍላጎቶች እንዲኖሩት እና አዲስ ጓደኞች እንዲያፈራ ያበረታቱት።
- የልጅዎን ጓደኞች እና ሁልጊዜ እሱ/እሷ የት እንዳለ/እንዳለች ይወቁ።
- ለተማሪዎ እገዛ ለማድረግ ወይም ለማዳመጥ፣ እና በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ ከጎኑ እንደሚሆኑ በተደጋጋሚ ያስታውሱ።
- ተማሪዎ የእሱን/የእሷን አማካሪ እንዲያውቁ ያበረታቱ።
- ትምህርት ቤት ውስጥ በወላጆች ስብሰባ በመሳተፍ እንዴት ለትምህርት ቤት በጎ ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ይወቁ።
- ትምህርት ቤት ውስጥ የእርስዎን ተማሪ ጥረቶች በቀጣይነት እውቅና በመስጠት ይሸልሙ።

# ጠቃሚ የድረገጽ ማስፈንጠሪያዎች

## [www.apsva.us](http://www.apsva.us)

ስለሚከተሉት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **ወደ APS ድህረ ገጽ "ምዝገባ" ክፍል** ይሂዱ።

- የምዝገባ ሂደት እና ቅጾች
- አማራጮች እና ዝውውሮች
- የትምህርት ቤት ወሰኖች
- የቋንቋ አገልግሎቶች ምዝገባ ማዕከል (እንግሊዘኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ወይም ከሃገር ውጪ ትምህርት ሲማሩ ለነበሩ ተማሪዎች)

ስለሚከተሉት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ **APS ድህረ ገጽ "ፕሮግራሞች/አገልግሎቶች" ክፍል** ይሂዱ።

- የአካዳሚክ እቅድ ማውጣት
- የማማከር አገልግሎቶች
- ብዝሃነት፣ ፍትሃዊነት እና አካታችነት
- የተራዘመ ቀን (መግቢያ) ፕሮግራም
- የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳታፊነት (FACE)
- የወላጅ መርጃ ማዕከል (PRC)
- ልዩ ትምህርት

ስለ ትምህርት ቤት ፖሊሲዎች የበለጠ ለማወቅ
ወደ **APS ድህረ ገጽ "የትምህርት ቤት ቦርድ" ክፍል** ይሂዱ

- ፖሊሲ J-5.3.30፡ ቅበላ እና ምደባ
- ፖሊሲ J-5.3.31፡ አማራጮች እና ዝውውሮች

ለሚከተለው **የ"ቤተሰቦች" ማስፈንጠሪያን በAPS ዋና ገጽ** ላይ ይጎብኙ፡

- የወላጅ VUE ማስፈንጠሪያ
- የምሳ ምናሌ እና ነጻ እና ቅናሽ ምግብ ማመልከቻ
- የወላጅ አካዳሚ (ለወላጆች ነጻ ኮርሶች)
- የ APS መምሪያና ሌላ መረጃ

# ማውጫ

**ዶሮቲ ሃም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ኤለን ስሚዝ፣ ርዕሰ መምህር**
4100 Vacation Lane, 22207
703-228-2910
dorothyhamm.apsva.us

**ጉንስተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ዶክተር ሎሪ ዊጊንስ፣ ርዕሰ መምህር**
2700 South Lang Street, 22206
703-228-6900
gunston.apsva.us

**H-B ዉድላውን ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራም (ከ6-12 ክፍሎች)**
**ዶክተር ኬሲ ሮቢንሰን፣ ርዕሰ መምህር**
1601 Wilson Boulevard., 22201
703-228-6363
hbwoodlawn.apsva.us

**ቶማስ ጀፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ኬኻ ቦጋን፣ ርዕሰ መምህር**
125 South Old Glebe Road, 22204
703-228-5900
jefferson.apsva.us

**ኬንሞር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ዴቪድ ማክብራይድ፣ ርዕሰ መምህር**
200 South Carlin Springs Road, 22204
703-228-6800
kenmore.apsva.us

**ስዋንሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ሬኒ ሃርበር፣ ርዕሰ መምህር**
5800 North Washington Boulevard, 22205
703-228-5500
swanson.apsva.us

**ዊሊያምስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**
**ብሪያንቦይኪን፣ ርዕሰ መምህር**
3600 North Harrison Street, 22207
703-228-5450
williamsburg.apsva.us

# APS መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦታዎች እና ወሰኖች




ማጣቀሻ

ካውንቲአቀፍ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የመሃከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የመሃከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወሰኖች

ማይል

0 1 2 4

ማሳሰቢያ፡
የአካባቢዎን ትምህርት ቤት የእኛን የቦታ መፈለጊያ በመጠቀም ለመወሰን ከፈለጉ፣ ወደ APS (www.apsva.us) የ“ምዝገባ” ክፍል ይሂዱ።
ለበለጠ መረጃ፣ የትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን በ703-228-6005 ያግኙ።